ውድ ወላጅ ወይም አሳዳጊ፣

በፕሮግራማችን ወይም በማህበረሰቡ ውስጥ የኩፍኝ ወረርሽኝ ከተከሰተ ምን ሊፈጠር እንደሚችል ዕድሜያቸው ከ12 ወር በታች የሆኑ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች ሁሉ እንዲያውቁ እንፈልጋለን።

የኩፍኝ ወረርሽኝ ከተከሰተ፣ የኩፍኝ በሽታ የመከላከል አቅም (መከላከያ) ማረጋገጫ ማቅረብ የማይችል ማንኛውንም ሰው ለበሽታው ከተጋለጠበት የመጨረሻ ጊዜ ጀምሮ **እስከ 21 ቀናት ድረስ ቤት ውስጥ እንዲቆይ** የጤና ጥበቃ መምሪያ ሊያስገድድ ይችላል። ይህም የኩፍኝ በሽታ ስርጭትን ለማስቆም ይረዳል።

አብዛኛዎቹ ልጆች በሽታ የመከላከል አቅምን የሚያዳብሩት በአብዛኛው ከልጁ አንደኛ ዓመት ልደት በኋላ በሚሰጠው **measles, mumps, and rubella (MMR፣ የኩፍኝ፣ ጆሮ ደግፍ እና ሩቤላ)** ክትባት አማካኝነት ነው። **ልጅዎ ዕድሜው ከ1 ዓመት በታች በመሆኑ፣ ቤት ውስጥ መቆየት ሊያስፈልገው ይችላል።**

ስለ ኩፍኝ በሽታ እና ስለ MMR ክትባት መርሃ ግብር ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት ከጤና እንክብካቤ ባለሙያዎ ጋር እንዲነጋገሩ እናበረታታዎታለን።

ኩፍኝ በጣም ተላላፊ ነው እንዲሁም በፍጥነት ሊሰራጭ ይችላል። በተጨማሪም ከባድ የጤና ችግሮችን ሊያስከትል ይችላል። ለበለጠ መረጃ፣ እባክዎን የWashington State Department of Health (የዋሽንግተን ስቴት የጤና መምሪያን) ይጎብኙ፦ doh.wa.gov/measles።

ከሰላምታ ጋር፣